ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
FEDERAL SUPREME COURT

መዝገብ ቁጥር216115

ቀን፡ መጋቢት 08/2014 ዓ.ም

ለኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ

<u>አ/አ</u>

ይግባኝ ባይ ብልፅግና ፓርቲ እና በመልስ ሰጪ እነ የኢትዮጵያ ሶሻል ዲሞክራሲ ፓርቲ መካከል ባለው የፍትሐብሔር ክርክር ጉዳይ ፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት 2ኛ ፍታሐብሔር ችሎት መጋቢት 07 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ 14 ገጽ ትክክል ግልባጭ ከዚህ መሸኛ ጋር የላክን መሆኑን እንገልፃለን፡፡

አሥራት ማሙዬ ቸርታው
የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሬጂስትራር

ፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፍ/ብሔር 2
Federal Supreme Court The Federal Democratic Republic of Ethiopia

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ
ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የይ/መ/ቁጥር 216115

መጋቢት 07 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተሾመ ሽፈራው

ኑረዲን ከድር

ሀብታሙ እርቅይሁን

ይግባኝ ባይ፡-ብልፅግና ፓርቲ ጠበቃ አሊ መሀመድ ቀረበ

መልስ ሰጪዎች፡-1. የኢትዮጲያ ሶሻል ዲሞክራቲክ ፓርቲ አልቀረቡም

2. የኢትዮጲያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ወንጌል አባተ ቀረበ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን በዚሁ አግባብ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ይህ የይግባኝ አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው የኢትዮጲያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ጥቅምት 01 ቀን 2014 ዓም የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እንዲህ ነው፡-1ኛ መልስ ሰጪ በደቡብ ብ/ብ/ህ/ብ/ክ/መንግስት መስከረም 20 ቀን 2014 ዓም በተደረገው 6ኛው አገር አቀፍ ምርጫ በሌሞ 01 ምርጫ ክልል በተለያዩ የምርጫ ጣቢያዎች ከድምፅ አሰጣጥ፤ቆጠራ እና ውጤት መደመርን በሚመለከት የተለያዩ ጥሰቶች ተፈፅመዋል በማለት ያቀረበውን አቤቱታ እና ማስረጃዎች በመመርመር 2ኛ ተጠሪ በሰጠው ውሳኔም በሌሞ 01 የምርጫ ክልል ውጤት እንዲሰረዝና በድጋሚ ምርጫ እንዲከናወን ወስኗል፡፡

ይግባኝ ባይ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ህዳር 03 ቀን 2014 ዓም በተፃፈ ባቀረበው የይግባኝ አቤቱታም 1ኛ መልስ ሰጪ በምርጫው ቀን በምርጫ ክልሉ ተፈጥረዋል በማለት የዘረዘራቸውን ችግሮችና የስነምግባር ጥሰቶች በእለቱ ወዲያውኑ ችግሩ ለታየበት የምርጫ ጣቢያ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴና ለሌሞ 01 ምርጫ ክልል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በማቅረብ በአዋጁ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 54፤122፤154 እና 155 እንዲፈቱ ማድረግ ሲገባው ይህንን በማድረግ በተገቢው ጊዜና ቦታ ማጣራት እንዲደረግባቸው ያላደረገ በመሆኑ ከዚህ ይልቅ 1ኛ መልስ ሰጪ አቤቱታውን ለቦርዱ ያቀረበው በአዋጁ አንቀፅ 118 መሰረት በ1ኛ መልስ ሰጪ የተመደቡት የምርጫ ወኪሎች፤የይግባኝ ባይ የምርጫ ወኪሎች፤የሌሎች በምርጫ ክልሉ የተወዳደሩ የፖለቲካ ድርጅቶች ወኪሎች፤የምርጫ አስፈፃሚዎች እና በቦርዱ እውቅናና ፈቃድ



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
The Federal Supreme Court
ፍ/ብሔር 2
ፌዴ/ ጠ ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ቀን 8/7/2014

የተሰጣቸው ገለልተኛ የምርጫ ታዛቢዎች ምርጫው የሁሉንም መራጮችና እጩ ተወዳዳሪዎች መብትና ነፃነት በተከበረበት፣የእኩልነትና የሚስጥር ድምፅ አሰጣጥ ስርዐት በተጠበቀበት የምርጫ ህጉን መሰረት ባደረገ መንገድ የተከናወነ ለመሆኑ አረጋጠው ቃለ ጉባዔ ይዘው ተፈራርመው መራጮች የሰጡት ድምፅ በህጉ አግባ ተቆጥሮ ውጤቱ ከተለጠፈ በኋላ በመሆኑ ይህም 1ኛ መልስ ሰጪ ቅሬታውን ያቀረበው በእለቱ የተፈጠረ ችግርና እና የስነ ምግባር ጥሰት በመኖሩ ሳይሆን በምርጫው ውጤት ባለመደሰት መሆኑን እያሳየ 2ኛ መልስ ሰጪ ቅሬታው ለተገቢው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ቀርቦ ተገቢው ማጣራት የተደረገበት አለመሆኑን በመጥቀስ ውድቅ ሊያደርገው ሲገባ በይግባኝ አይቶ መወሰን ያለበትን ጉዳይ በቀጥታ ተቀብሎ አዋጁ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 54፣122፣154 እና 155 ተገቢውን ማጣራት ሳያደርግ የሰጠው ውሳኔ በአዋጁ የተመለከተውን የተላለፈ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ሊሻር ይገባል፤

ቦርዱ ጉዳዩን በቀጥታ ዳኝነት የማየት ስልጣን አለኝ የሚል ከሆነም አቤቱታው በህግ በተደነገገው አግባብ ተፈፀሙ የሚላቸውን የስነምግባር ጥሰቶች፣የተፈጸመበትን የምርጫ ጣቢያ የተፈፀመበትን ሰአት ቦታና ሁኔታ እንዲሁም ጥሰቶቹን የፈፀመውን ማንነት እውነታውን ለማጣራት በሚያስችል መንገድ ያልቀረበ በመሆኑ አቤቱታውን የምርጫ ህጉ በሚደነግገው መሰረት አሻሽሎና ግልፅ አድርጎ እንዲያቀርብ ሊያደርግ ሲገባ 1ኛ መልስ ሰጪ በ25/01/2014 ዓም የሞላውን ጥቅልና ግልፅነት የጎደለው እርስ በእርሱ የሚቃረን ፎርም በመቀበል የሰጠው ውሳኔ ህጋዊ መሰረት የሌለው በመሆኑ ሊሻር ይገባል፤ለ2ኛ መልስ ሰጪ ህግ አውጪው በአዋጅ ቁጥር 1133/2011 እና በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀፅ 155 (3) እና በሌሎች ድንጋጌዎች የተሰጠው ከፊል የዳኝነት ስልጣን ሆኖ እያለ 1ኛ መልስ ሰጪ ያቀረበለትን ጉድለት ያለበት አቤቱታ ተቀብሎ ውሳኔ የሰጠው ለይግባኝ ባይ እንዲደርሰውና ተፈፅሙዋል የተባሉ የስነ ምግባርና የህግ ጥሰቶች አውቆ እውነታውን የማስረዳትና የመከላከል መብቱን ሳይጠብቅ መሰረታዊ የሆነውን የቀረበብኝን ክስ የማወቅ፣የመከላከል፣የመልስ ሰጪን ማስረጃ እና ምስክሮች የመመርመር፣በመስቀለኛ ጥያቄ እውነታውን የማውጣት ፣የመከላከያ ማስረጃ የማቅረብ እና የማሰማት መብቴን በመጣስ የህገ መንግስቱን አንቀፅ 13(2)፣37(1) እና አለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች አንቀፅ 14(1) ን በመተላለፍ የተሰጠ በመሆኑ ሊሻር ይገባዋል፤

1ኛ መልስ ሰጪ በ21/01/2014 ዓም ያቀረበው ማመልከቻ በከንተብ 01 የምርጫ ክልል፣በከንተብ 02 የምርጫ ክልል እና በሌሞ 01 የምርጫ ክልል ተፈፅመዋል የሚላቸውን የስነምግባር ጥሰቶች በመዘርዘር ቢሆንም ያቀረባቸው የሰነድ ማስረጃዎች ግን የሌሞ 01 የምርጫ ክልልን የሚመለከቱ ባልሆኑበት፣ቀርበው የተሰሙት ሁለት ምስክሮች የሰጡት የምስክርነት ቃልም አብዛኛው የሌሞ 01 ምርጫ ክልልን የሚመለከት ሳይሆን ከንተብ 01 እና ከንተብ 02 የምርጫ ክልልን የሚመለከት ሆኖ እያለ ማስረጃዎቹን በተሳሳተ መንገድ በመረዳት የሰጠው ውሳኔ የፍሬ ጉዳይ እና የማስረጃ ምዘና ስህተት ያለበት በመሆኑ ውሳኔው ሊሻር ይገባል፤

Federal Supreme Court

ፍ/ብሔር 2

2ኛ መልስ ሰጪ 1ኛ መልስ ሰጪ ያቀረበውን አቤቱታና ማስረጃ እውነትነት ያለው መሆኑን ወይም አለመሆኑን ከራሱና በየደረጃው ካቋቋማቸው የምርጫ አስፈፃሚዎች ህጋዊ ሰነዶች ጋር ሳያገናዝብ እና ሳይመረምር ወይም ገለልተኛ የሆኑ ባለሙያዎችን መድቦ ሳያጣራ አቶ ያዕቆብ አኖሬ እና አቶ ጋሻው እሳቱ የተባሉት ምስክሮች 1ኛ መልስ ሰጪ ምርጫውን እንዲከታተሉና እንዲታዘቡለት ወኪል አድርጎ የመደባቸው መሆኑን ሳያረጋግጥ ፤ምስክሮቹ በሌሞ 01 የምርጫ ክልል ምርጫውን በወኪልነት ያልታዘቡና ያልተከታተሉ ሆነው እያለ አቶ ያዕቆብ አኖሬ የከንተብ 01 ምርጫ ክልል እጩ ተወዳዳሪ ሆነው እያለ ወኪል አድርጎ እንደተመደቡ በማድረግ የሰጡትን የሀሰት የምስክርነት ቃል ተቀብሎ የሰጠው ውሳኔ ህጉን መሰረት ያላደረገ በመሆኑ ሊሻር ይገባል፤

ምርጫው የህገ መንግስቱን እና የምርጫ ህጉን ድንጋጌዎች መሰረት በማድረግ የተከናወነ መሆኑን የ1ኛ መልስ ሰጪ እና የሌሎች ተወዳዳሪ የፖለቲካ ድርጅቶች ተወካዮች፤ገለልተኛ የምርጫ ታዛቢዎች እና በየደረጃው ያሉ የምርጫ አስፈፃሚዎች በቃለ ጉባዔ እና በፊርማቸው ያረጋገጡት እውነታ ሆኖ እያለ፤ይግባኝ ባይ በዝርዝር ያቀረባቸው ዝርዝር ማስረጃዎችም ይህንኑ እያሳዩ፤ 2ኛ መልስ ሰጪ የ1ኛ መልስ ሰጪና አቤቱታና ማስረጃዎች ከራሱና በየደረጃው ካቋቋማቸው የምርጫ አስፈፃሚዎች ህጋዊ ሰነዶች ጋር ሳያገናዝብ እና ሳይመረምር ወይም ገለልተኛ የሆኑ ባለሙያዎችን መድቦ ሳያጣራ ለጉዳዩ ገለልተኛ ያልሆኑ እና ስለሁኔታው የማያውቁ ሁለት ምስክሮች የሰጡትን ሀሰተኛ የምስክርነት ቃል ብቻ በማመን ይግባኝ ባይ በምርጫ ክልሉ ያገኘው ውጤት እንዲሰረዝ የሰጠው ውሳኔ ጉልህ የሆነ የፍሬ ጉዳይ፤የማስረጃ ምዘናና የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊሻር ይገባል፤

1ኛ መልስ ሰጪ ስማቸውን ጠቅሶ አቤቱታ ያቀረበባቸው 5 የምርጫ ጣቢያዎች ሲሆኑ ምስክሮቹ ያላዩትን አይተናል፤በስሚ ስሚ ተነግሮናል በማለት የምስክርነት ቃል የሰጡት በ43 ምርጫ ጣቢያዎች ሲሆኑ ያስረዱትም በአቤቱታው ላይ የተገለፁት የስነምግባር ጥሰቶች መፈፀማቸውን በመዘርዘር ሳይሆን 43 ምርጫ ጣቢያዎችን በመጥቀስ ሲሆን ጥሰቶቹ መፈፀማቸውን የሚገልፅ ዝርዝር ማስረጃ በማቅረብ 1ኛ መልስ ሰጪ የማስረዳት ሸክሙን ባልተወጣበት በምርጫው ክልል ያሉ ጣቢያዎች 138 ሆነው እያለ ቦርዱ ቢበዛ የ43 ምርጫ ጣቢያዎች ሊሰርዝ ሲገባ ከዚህ በማለፍ ሁለት ሶስተኛ በሚሆኑት 95 ምርጫ ጣቢያዎች ላይ መራጮች የሰጡትን ድምፅ ይግባኝ ባይ ከፍተኛ የሆነ የመራጮች ድምፅ 1ኛ መልስ ሰጪ ደግሞ ዝቅተኛ የመራጮች ድምፅ ማግኘቱን በንፅፅር በውሳኔው ላይ አመልክቶ የምርጫው ውጤት ያለምክንያት እንዲሰረዝ ውሳኔ መስጠቱ የህግ መሰረት የሌለው በመሆኑ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ይግባኝ ባይ ያቀረባቸውን እውነታውን የሚያስረዱ የሰነድ ማስረጃዎች በመቀበልና በመመርመር ገለልተኛ የሆኑ ምስክሮችን ቃል በመስማት እውነታውን በማጣራት የቦርዱን ውሳኔ በመሻር ውሳኔ ይስጥልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

Federal Supreme Court
Federal Democratic Republic of Ethiopia

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ

2ኛ መልስ ሰጪ በሌሞ 01 የምርጫ ክልል ምርጫው እንዲደገም የወሰነው የ1ኛ መልስ ሰጪ ቅሬታ ተገቢውን የቅሬታ ማቅረቢያ ስርዐት አልፎ የቀረበ መሆኑን አረጋግጦ ነውን?2ኛ መልስ ሰጪ ውሳኔውን የሰጠው በሚሰጠው ውሳኔ መብታቸው የሚነካ አካላትን ወደ ክርክሩ እንዲገቡ በማድረግ በአግባቡ አከራክሮና ጥሰቱ ስለመኖሩ በተገቢው ማስረጃ አረጋግጦ ነውን? የሚሉትንና ተያያዥ ነጥቦችን ለማጣራት የይግባኝ አቤቱታው ያስቀርባል ከተባለ በኋላ ለ1ኛ መልስ ሰጪ መጥሪያ ደርሶት ህዳር 24 ቀን 2014 ዓም በተፃፈ ባቀረበው መልስም ቦርዱ ውሳኔውን የሰጠው ቅሬታችንን በአግባቡ በማጣራት የቅሬታችንን ተገቢነት በመቀበል በመሆኑ ውሳኔ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

2ኛ መልስ ሰጪ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.40(2) መሰረት በመልስ ሰጪነት ወደ ክርክሩ እንዲገባ ትዕዛዝ ተሰጥቶ መጥሪያ ደርሶት ህዳር 24 ቀን 2014 ዓም በተፃፈ ባቀረበው መልስም ከመነሻው የአዋጁ ድንጋጌ አቤቱታ አቅራቢው በታችኛው እርከን የሚገኙ መፍትሄ ሰጪ አወቃቀሮችን አሟጦ የመጠቀም (Exhaustion Of Remedies) ግዴታን ተግባራዊ ማድረግ የሚችልበት አወቃቀር ባልተዘረጋበት ሁኔታ ለሚቀጥለው አካል አቤቱታውን ማቅረብ አይችልም የሚል ትርጓሜ ሊሰጠው የማይገባ ሲሆን በታችኛው እርከን የምርጫ ማስፈፀሚያ አደረጃጀቶች የቅሬታ አፈታት አወቃቀር ባለመኖሩ መፍትሄ ማግኘት ባልቻለ አቤቱታ አቅራቢ ቅሬታ የቀረበለት ዋነኛ የምርጫ አስተዳዳሪው ከፍተኛ የውሳኔ ሰጪ አካል አቤቱታው ከበቂ ዝርዝርና ማስረጃ ጋር እንዲቀርብ በማድረግ ውሳኔ መስጠቱ በአግባብ ስለሆነ አመልካችም ሰኔ 14 ቀን 2013 ዓም ከተደረገው ጠቅላላ ምርጫ ጋር በተያያዘ በተመሳሳይ ጥያቄውን ለ2ኛ መልስ ሰጪ በማቅረብ እንዲመረመር አድርጎ እያለ ከአወቃቀሩ ጋር በተያያዘ ክርክር ማቅረቡ አግባብ ባለመሆኑ የይግባኝ ባይ ክርክር ውድቅ ሊደረግ ይገባል፤

2ኛ መልስ ሰጪ በአዋጁ አንቀፅ 151 የምርጫ አለመግባባቶችን ፍትሀዊ በሆነ መንገድ ለመፍታት ህግን መሰረት በማድረግ የሚዘረጋቸውን አወቃቀሮች የሚያመለክት ሲሆን በዚህ አግባብ አጣሪ አዋቅሮ ጥሰቶች እንዲጣሩ ማድረግ አንዱ አማራጭ ቢሆንም ይህንን ማድረግ ግዴታ አይደለም፤መልስ ሰጪ መስከረም 20 ቀን 2014 ዓም ከተደረገው ምርጫ ጋር በተያያዘ የቀረቡለትን ቅሬታዎች ከተመለከተ በኋላ በምርጫ የጊዜ ሰሌዳ እና አግባብነት ባለው የህግ ማዕቀፍ መሰረት ይፋዊ የምርጫ ውጤት ማሳወቅ ብሎም አቤቱታዎቹ ፍትሃዊ በሆነ መንገድ በአፋጣኝ የሚፈቱበትን አሰራር በስራ ላይ በማዋል ከ6 የፖለቲካ ፓርቲዎችና ከ29 የግል እጩዎች የቀረበለትን አቤቱታ ለመመርመር የሚያስችለው አወቃቀር በዋና ፅ/ቤት ደረጃ መስርቶ ተገቢ ነው ብሎ ያመነበትን ውሳኔ የሰጠ በመሆኑ 1ኛ መልስ ሠጪ በሌሞ 01 ተፈፅመዋል ያላቸውን ጥሰቶች ዘርዝሮ ያቀረበ ሲሆን ይህ አቤቱታ በአግባቡ ያልቀረበ በመሆኑ ለፍትሀዊ ውሳኔ አሰጣጥ አመቺ በሆነ መልኩ ሊቀርብ የሚችልበት እና ውሳኔ አሰጣጥን በአግባቡ የሚያሳልጥ የአቤቱታ ማቅረቢያ ቅፅ በማዘጋጀት ሁሉም ቅሬታ አቅራቢዎች ቅፁን በመሙላት እንዲያቀርቡ በማድረግ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡



Federal Supreme Court Federal Democratic Republic of Ethiopia ፍ/ብሔር 2

ጊዜን በተመለከተ ድምፅ አሰጣጡ፤ቆጠራውና ውጤቱ በአንድ ቀን የሚከናወን በመሆኑ የጊዜው መመልከት አለመመልከት መሰረታዊ የስነ ስርዐት ግድፈት ተደርጎ የሚወሰድ ባለመሆኑ፤ግልፅነት በጎደላቸው ቅፁ ላይ በተመለከቱት ነጥቦች ላይ ማስረጃ ከመሰማቱ በፊት ቅሬታ አቅራቢዎች ማብራሪያ እንዲሰጡ የተደረገ በመሆኑ ማስረጃዎቹ ተፈፅመዋል የተባትን ጥሰቶች ፤የተፈፀመበትን የምርጫ ጣቢያ እና ፈፃሚውን በበቂ ሁኔታ በተጨባጭ ያረጋገጡ በመሆኑና የሸፈኑት የምርጫ ጣቢያ መጠነ ሰፊ መሆን የምርጫ ክልሉን የምርጫ ውጤት በእጅጉ ሊያዛንፍ የሚችል መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ የቀረበው ቅሬታ ተቀባይነት አግኝቶ የምርጫ ክልሉ .ውጤት እንዲሰረዝና ምርጫው በድጋሚ እንዲካሄድ መወሰኑ በአግባቡ ስለሆነ የይግባኝ ባይ አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል፤

የፓርቲው ወኪሎች ከድምፅ አሰጣጥ፤ቆጠራናውጤት አገላለፅ ሂደት በተቀነባበረ ሂደት መገለላቸውና ያልተገባ ጫና የተደረገባቸው መሆኑ፤በመራጮች በነፃነት የመምረጥ መብት ላይ ያልተገባ ጣልቃ ገብነት የነበረ መሆኑ፤በምርጫ ጣቢያ መገኘት የማይችሉ የፀጥታ አካላት በምርጫ ጣቢያው ተገኝተውና የምርጫ አስፈፃሚዎችንም ተክተው የድምፅ ቆጠራ ተግባራትን ማከናወናቸው እነዚህ ድርጊቶች የምርጫውን ውጤት ሊያዛንፉ የሚችል ቁጥር ባላቸው የምርጫ ጣቢያዎች ስለመፈፀማቸው በተጨባጭ ማስረጃ ተረጋግጦ የተሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ስለሆነ ሊፀና ይገባል፤2ኛ መልስ ሰጪ ጉዳዩን በሚመረምርበት ጊዜ ለጉዳዩ አግባብነት ላቸው ያላቸውን ማስረጃዎች ሁሉ አስቀርቦ የመረመረ ሲሆን በዚህ ሂደትም 1ኛ መልስ ሰጪ ያቀረባቸውን የፎቶ ግራፍ ማስረጃዎች በደጋፊ ማስረጃነት የተመለከተ ሲሆን ከሰው ማስረጃዎቹ በተጨማሪ የሰነድ ማስረጃዎችን በመመርመር የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ፤ከምርጫ አለመግባባቶች የተለየ ባህሪይ አንፃር በክርክሩ ተሳታፊ የሚሆኑ አካላትን ወሰን የመወሰን መብት ለ2ኛ መልስ ሰጪ በህግ የተሰጠው ስልጣን በመሆኑ በዚህ ውሳኔ ቅር የተሰኘ አካል በአዋጁ አንቀፅ 155(4) መሰረት ውሳኔው ከተሠጠበት ጊዜ ጀምሮ ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት  በ10 ቀን ውስጥ የይግባኝ ቅሬታ ማቅረብ በመሆኑ የይግባኝ ባይ የይግባኝ አቤቱታ ውድቅ ተደርጎ ውሳኔው ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በማስከተል ግራ ቀኙ በቃል እንዲከራከሩ የተደረገ ሲሆን ይግባኝ ባይ ባቀረቡት የተጨማሪ ማስረጃ አቤቱታ ላይ መልስ ሰጪዎች አስተያየት እንዲሰጡ በተሰጠው ትዕዛዝ 2ኛ መልስ ሰጪ ብቻ አስተያየቱን አቅርቦ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

የነገሩ አመጣጥና የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ እንደተመለከተው ሲሆን እኛም ጉዳዩን  በማስቀረቢያነት ከተያዘው ጭብጥ፤ለጉዳዩ አግባነት ካላቸው ድንጋጌዎችና ከግራ ቀኙ ክርክር  አንጻር መርምረናል፡፡በመሰረቱ በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የመንግሥት ሥልጣን መያዝ የሚቻለው በምርጫ ነው፡፡ የአንድ አገር ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ከሚለካባቸው መስፈርቶች ውስጥ ዋነኛው ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ በማካሄድ የሕዝቦችን ሉአላዊ የሥልጣን ባለቤትነት ማረጋገጥ ነው፡፡ ሕዝቦች በቀጥታ ወይም በነፃነት በሚመርጧቸው ተወካዮቻቸው አማካኝነት በሕዝብ ጉዳይ አስተዳደር የመሳተፍ መብት ያላቸው ሲሆን



ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ቀን 8/12/2011
ፍ/ብሔር 2
Federal Supreme Court
The Federal Democratic Republic of Ethiopia

ይህንን መብት በተግባር ለማረጋገጥ ደግሞ በየጊዜው የሚከናወንና ሂደቱም ነፃ ሁሉን አቀፍ፣ ትክክለኛ፣ ቀጥተኛ፣ በእኩልነት ላይ የተመሠረተና በሚስጥር የሚከናወን የምርጫ ሥርዓት መገንባት አስፈላጊ ነው፡፡ ምርጫ በማንኛውም መልኩ ከማጭበርበር የፀዳና የመራጩ ሕዝብ ድምጽ የሚከበርበት መሆን አለበት፡፡

በምርጫ ሂደት በሕግ የመራጭነት መብት የተሰጣቸው መራጮች የወደፊት ተወካዮቻቸውን በሚመርጡበት ጊዜ የመምረጥ መብታቸው ሙሉ በሙሉ የተከበረ መሆን አለበት፡፡ ነገር ግን ምርጫ በሚካሄድበት ጊዜ በምርጫ ሂደት እንደማንኛውም ጉዳይ በተለያዩ ምክንያቶች አቤቱታዎችና ቅሬታዎች ይኖራሉ፡፡ እነዚህን ቅሬታዎችና አቤቱታዎች በሕግ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ብየደረጃው ተገቢውን ውሣኔ የሚሰጡ አካላት ይኖራሉ፡፡ በምርጫ ወቅት የሚነሱ አለመግባባቶች ፍትሃዊ ውሣኔ ካላገኙ የሕዝቡን መብት የሚያሸራርፉ ከመሆናቸው በላይ ግጭት ሊፈጥሩ የሚችሉ ናቸው፡፡ በመሆኑም በተለያየ ምክንያት ለሚነሱ ቅሬታዎች የገለልተኝነት እና የግልጽነት መርህን መሠረት ባደረገ መልኩ በመምራት አጭር ጊዜ ውስጥ ፍትሐዊ ዉሳኔ መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ይህን ማድረግ ምርጫው ዲሞክራሲያዊ፣ ነፃና ፍትሐዊ እንዲሆን የሚያደርግ ከመሆኑም በላይ ምርጫ ነክ ግጭቶች እንዳይፈጠሩ የማድረግ ዉጤት ይኖረዋል፡፡

የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ስነምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 ከምርጫ ሂደት ጋር በተያያዘ የሚነሱት የተለያዩ አለመግባባቶች የሚፈቱባቸዉን ሥርዓቶች እንዲሁም ቅሬታዎችን ተቀብለዉ እልባት የሚሰጡ አካላትን ለይቶ ይደነግጋል፡፡ በዚህም መሠረት የምርጫ ጣቢያ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ፣ የምርጫ ክልል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ፣ የምርጫ ክልል ጽ/ቤት እና ምርጫ ቦርድ ሆነው ተመልክተዋል፡፡ እነዚህ አካለት በሚሰጡት ውሳኔ እንደ አግባብነቱ በይግባኝ ሆነ በአስተዳደራዊ ክለሳ ሥርዓት ጉዳዩ በፍርድ ቤት የሚስተናገድ ነው፡፡አሁን በያዝነው ጉዳይ 1ኛ መልስ ሰጪ በ2ኛ መልስ ሠጪ ቦርድ ቅሬታ ያቀረበባቸው የቅሬታ ነጥቦች በድምፅ አሰጣጥ ሂደት ተፈጠሩ ካላቸውና በድምፅ ቆጠራና ውጤት ከሚነሱ ክርክሮች ጋር የተያያዙ ሲሆኑ 2ኛ መልስ ሰጪ በ1ኛ መልስ ሰጪ የቀረበውን ቅሬታ ተቀብሎ ያስተናገደው በቅድሚያ ቅሬታው የምርጫ ጣቢያ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ፣ የምርጫ ክልል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ፣ እና የምርጫ ክልል ጽ/ቤት ተመልክተውት በህጉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ተገቢውን እልባት የሰጡ መሆኑን በማረጋገጥ ስለመሆኑ የቦርዱ ውሳኔ አያሳይም፡፡

2ኛ መልስ ሰጪ የ1ኛ መልስ ሰጪ ቅሬታ በተገቢው የቅሬታ አፈታት ስርዓት ያላለፈው ቅሬታው ለመቀበል መነሻ የሆነው የምርጫ ጣቢያ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በሌሞ 01 የምርጫ ክልል ባለመቋቋሙ ምክንያት መሆኑን በመጥቀስ የሚከራከር ሲሆን ፤ይግባኝ ባይ በበኩሉ የሌሞ 01 ምርጫ ክልል ፅ/ቤት ህዳር 29 ቀን 2014 ዓም ለይግባኝ ባይ የፃፈውን ደብዳቤ መነሻ በማድረግ የቅሬታ ሰሚ አደረጃጀቱ በሁሉም የምርጫ ጣቢያዎችና የምርጫ ክልሎች የነበረ መሆኑን በመጥቀስ የ2ኛ መልስ ሰጪ ክርክር አግባብነት የለውም በማለት ክርክሩን አቅርቧል፡፡



The Federal Democratic Republic of Ethiopia Federal Supreme Court

በኢትዮጲያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ የሌሞ 01 ምርጫ ክልል ፅ/ቤት ለይግባኝ ባይ ህዳር 29 ቀን 2014 ዓም የፃፈው ደብዳቤ የቅሬታ ሰሚ አደረጃጀቱ በሁሉም የምርጫ ጣቢያዎችና የምርጫ ክልሎች የነበረ መሆኑን የሚገልፅ ቢሆንም ይህ አደረጃጀት ሰኔ 14 ቀን 2013 ዓም በመደበኛ ሁኔታ በሀገር አቀፍ ደረጃ ከተደረገው ምርጫ ባሻገር አከራካሪው የሌሞ 01 ምርጫ በምርጫ ክልሉ ዘግይቶ መስከረም 20 ቀን 2014 ዓም ሲደረግ ይኸው አደረጃጀት የምርጫውን ዘግይቶ መካሄድ መሰረት በማድረግ የተፈጠረ መሆኑን በዝርዝርና በግልፅ አያሳይም፡፡ከዚህም በተጨማሪ 6ኛው ሀገራዊ ምርጫ ሰኔ 14 ቀን 2013 ዓም ከተደረገ በኋላ የምርጫ ክልል ሀላፊዎችን ከጥቅምት 15 ቀን 2014 ዓም ጀምሮ የስራ ውላቸውን በማቋረጥ ሀላፊነታቸውን ቀሪ ያደረገ መሆኑን በመጥቀስ በኢትዮጲያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ የሌሞ 01 ምርጫ ክልል ፅ/ቤት ለይግባኝ ባይ ህዳር 29 ቀን 2014 ዓም የፃፈው ደብዳቤ ስልጣን በሌላቸው ግለሰብ የተፃፈ በዚህ አግባብም በማስረጃነት ሊቀርብ የማይገባ መሆኑን በመጥቀስ ክርክሩን ያቀረበ ቢሆንም ይግባኝ ባይ ደብዳቤውን አቶ ኢሳያስ እንዳለ ህዳር 29 ቀን 2014 ዓም ሲፅፉ በምርጫ ክልሉ በሀላፊነት የነበሩ በዚህ አግባብም ደብዳቤውን ለመፃፍ የሚያስችል ስልጣን ያላቸው መሆኑን በመጥቀስ ያቀረበው ክርክርና ማስረጃ የለም፡፡

ይህም በሌሞ 01 የምርጫ ክልል የምርጫ ጣቢያ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ፣ የምርጫ ክልል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ እና የምርጫ ክልል ጽ/ቤት የቅሬታ ሰሚ አደረጃጀቶች 1ኛ ተጠሪ ቅሬታውን ባቀረበበት ወቅት በአግባቡ የተዘረጉ ናቸው በማለት ይግባኝ ባይ ያቀረበው ክርክር በተገቢው ማስረጃ ያልተደገፈ መሆኑን ያሳያል፡፡ከላይ የተመለከቱት የቅሬታ ሰሚ አደረጃጀቶች በ2ኛ መልስ ሰጪ እንደታመነው በምርጫ ክልሉ ካልተቋቋሙ ደግሞ 1ኛ መልስ ሰጪ ተገቢውን የቅሬታ አቀራረብ ስርዓት አሟጦ ሳይጠቀም ቅሬታውን ለ2ኛ መልስ ሰጪ አቀረበ ተብሎ የ1ኛ መልስ ሰጪን ቅሬታ አቅርቦ ለጉዳዩ ተገቢውን እልባት የማግኘት መብት በሚያጣብብ መልኩ የይግባኝ አቤቱታው ውድቅ የሚደረግበት የሕግ አግባብ አይኖርም፡፡በአጠቃላይ 2ኛ መልስ ሰጭ ቅሬታው በምርጫ ጣቢያ እና በምርጫ ክልሎች ደረጃ የቀረበ ባይሆንም ለቦርዱ በቀጥታ የቀረበውን የይግባይን ቅሬታ ተቀብሎ ማስተናገዱ በኢፌዴሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 37 በተመለከተው አግባብ የሠዎች ፍትሕ የማግኘት መብትን ያከበረ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በግራ ቀኙ ሰፊ ክርክር የተደረገበትን በይግባኝ ባይ የቀረበውን ሁለተኛ የቅሬታ ነጥብ በተመለከተ እየአንዳፍትሕ ለማግኘት አቤቱታ የሚያቀርብ ወገን የሚያቀርበው አቤቱታ በቂ ዝርዝር ያለውና ጉዳዩን የሚመረምረውና ተገቢውን ውሳኔ የሚሰጠው አካል ትክክለኛ ፍትሕ ጋር እንዲደርስ በሚያስችል መልኩ በማቅረብ ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጡ የበኩሉን ግዴታ መወጣት ይኖርበታል፡፡ አቤቱታ ሲቀርብ ለአቤቱታው መነሻ የሆኑ ፍሬ ነገሮች በዝርዝር ተመልክተው፣ ጉዳዮችን የሚያስረዳ ማስረጃ እና አቤቱታው የቀረበለት አካል ውሳኔ ለመስጠት በሚያስችለው አግባብ ሊሆን ይገባል፡፡ ቅሬታ አቅራቢ የሚያቀርበው ቅሬታ በፅሁፍ ትክክለኛ ውሳኔ ለመስጠት በሚያስችል መልኩ ግልፅ ሆኖ ቦርዱ ለዚሁ ተግባር



The Federal Supreme Court
Federal Democratic Republic of Ethiopia
ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ቀን 8/4/2014

በሚያዘጋጀው ቅፅ ተዘጋጅቶ መቅረብ ያለበት መሆኑን በምርጫ ሂደት በየደረጃው ስለሚኖር ቅሬታ አቀራረብ ፤ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አደራጃጀት እና አሰራር መመሪያ ቁጥር 10/2013 በአንቀፅ 23 መደንገጉም ይህንን ግብ ለማሳካት እንዲቻል መሆኑን ከድንጋጌው ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡

አሁን በያዝነው ጉዳይ 1ኛ መልስ ሰጪ ቅሬታውን ለ2ኛ መልስ ሰጪ ያቀረበው መስከረም 21 ቀን 2014 ዓም በእጅ ፅሁፍ በተዘጋጀ ማመልከቻና መስከረም 25 ቀን 2014 ዓም በአቤቱታ ማቅረቢያ ቅፅ አማካኝነት ቢሆንም በቅፁ አማካኝነት በቀረበው አቤቱታ ላይ ሄጦ 07፤08/09 በመራጮች ላይ ወከባና ማስፈራራት መፈፀሙን በግልፅ ከማመልከቱ ውጪ ሌሎች ጥሰት ናቸው በማለት የገለፃቸው ድርጊቶች በየትኛው የምርጫ ጣቢያ እንደተፈፀሙ ቅፁ አያሳይም፡፡ መስከረም 21 ቀን 2014 ዓም የተዘጋጀው አቤቱታም ቢሆን በመግቢያው ላይ የከንተብ 01፤የከንተብ 02 እና የሌሞ 01 የምርጫ ክልል ቅሬታዎች በግልፅ መለያ ሳይቀመጥ በአንድ ላይ የተመለከተበት ከመሆኑም በተጨማሪ በሌሞ 01 ምርጫ ክልል ፈፀሙ የተባሉ ጥሰቶች የተመለከቱበት የአቤቱታው ገፅ 4 እና 5 በሄጦ 01፤08 እና 09 ምርጫ ጣቢያዎች ተፈፅሟል ያላቸውን ጥሰቶች በተራ ቁጥር 2 እና 3 ከማመልከቱ እና በተራ ቁጥር 4 የተመለከተው ድርጊት በሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች የተፈፀመ መሆኑን በደፈናው ከማመልከት ውጪ በተራ ቁጥር 1፤5 እና 6 የተመለከቱት ጥሰቶች በየትኛው የምርጫ ጣቢያ እንደተፈፀመ አቤቱታው በግልፅ አለማሳየቱ ከመነሻውም ከላይ በተመለከተው አግባብ አቤቱታው ትክክለኛ ውሳኔ ለመስጠት በሚያስችል መልኩ ግልፅ ሆኖ አለመቅረቡን ያሳያል፡፡

ቦርዱ የቀረበለትን አቤቱታ በመመርመር ማስረጃዎችን ሰምቶ የደረሰበትን መደምደሚያ በተመለከተም ከምርጫ ጋር የተያያዙ ቅሬታዎች በአጭር ጊዜ ግን ፍትሐዊና ውጤታማ በሆነ አግባብ እልባት ማግኘት ያለባቸው ሲሆን በምርጫ ወቅት የሚነሱ አለመግባባቶች ፍትሃዊ ውሳኔ ካላገኙ የሕዝቡን መብት የሚሸራርፉ ከመሆናቸውም በላይ ግጭት ሊፈጥሩ የሚችሉ በመሆናቸው ፍርድ ቤቶች በተለይም ከጥሰት ጋር በተያያዘ ቅሬታ ቀርቦላቸው የሚደርሱበት መደምደሚያ ከመራጮች እና እጩዎች መብት እንዲሁም ከጠቃላይ የህዝብ ጥቅም አንፃር ተፅዕኖው የጎላ በመሆኑ ፍርድ ቤቶች የምርጫ ህግ ጥሰት ተፈፅሟል የሚል መደምደሚያ ላይ ለመድረስ ግልፅና አሳማኝ (Clear and Convincing) ማስረጃ የቀረበላቸው መሆኑን ሊያረጋግጡ ይገባል፡፡

አቤቱታ ማቅረብ የቅሬታ አቅራቢው መብት ቢሆንም በአቤቱታው የተገለጸውን ፍሬ ነገር የማስረዳት ኃላፊነትና ግዴታም የአቤቱታ አቅራቢው በመሆኑ በዚህ አግባብም1ኛ መልስ ሰጪ መራጮች መደለያ ይሰጣቸው የነበረ መሆኑን፤በምርጫ አስፈፃሚዎች ጫና ሲደረግባቸውና ወከባና ማስፈራራት በተለያዩ አካላት ሲፈፀምባቸው የነበረ መሆኑን፤የፓርቲው ወኪሎች እንዳይታዘቡ ከምርጫ ጣቢያ የተባረሩ መሆኑን፤የውጤት መተማመኛ ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆንና የምርጫውን ሚስጥራዊነት አለመጠበቅ



ፌ/ጠ/ፍ/ቤት
The Federal Supreme Court
Federal Democratic Republic of Ethiopia

በወቅቱ የነበሩ መሰረታዊ ጥሰቶች መሆናቸውን በመግለፅ ቅሬታ ያቀረቡ በመሆኑ እነዚህ ጥሰቶች በእርግጥም የተፈፀሙ መሆኑን ሊያስረዳ ይገባል፡፡

የ1ኛ መልስ ሰጪ ምስክሮች በዚህ አግባብ የሰጡትን የምስክርነት ቃል ስንመረምረውም 1ኛ ምስክር በመሆን የቀረቡት አቶ ያዕቆብ አኖሬ በሌሞ 01 የምርጫ ክልል ተንቀሳቃሽ ወኪል እንዲሁም 2ኛ ምስክር አቶ ጋሻውን እሳቱ የፓርቲው ወኪል መሆናቸውን በመግለጽ ከጥሰቱ ጋር በተያያዘ መረጃዎቻቸው በቀጥታ የተመለከቱትና በወኪልነታቸው ከተለያዩ ወኪሎች ያገኟቸው መሆኑን በመግለፅ የምስክርነት ቃላቸውን የሰጡ ቢሆንም ከዚህ በተጨማሪም የማጣሪያ ምስክሮቹ አቶ ኤርዶ ሸሂቦ እና አቶ አዲሴ አውቶ እንደቅደም ተከተላቸው የፓርቲው ተዘዋዋሪና ተቀማጭ ወኪል መሆናቸውን በመጥቀስ ያስረዱ ቢሆንም ከዚህ ይልቅ የ1ኛ መልስ ሰጪ 1ኛ እና 2ኛ ምስክሮች በከንተብ 01 የምርጫ ክልል እጩ ተወዳዳሪ መሆናቸውን እንዲሁም የማጣሪያ ምስክሩ አቶ አዲሴ አውቶ በሶሮ 01 የምርጫ ክልል እጩ ተወዳዳሪ መሆናቸውን የሚያሳይ ማስረጃ በይግባኝ መቅረቡና ለዚህ ማስረጃ ማስተባበያ ክርክርም ሆነ ማስረጃ በተጠሪዎች አለመቅረቡ ምስክሮቹ የሰጡትን የምስክርነት ቃል አጠራጣሪ በሚያደርግ መልኩ በተለይም 2ኛ ምስክርና የማጣሪያ ምስክሩ ከመነሻውም በወቅቱ ያለውን እውነተኛ ተሳትፎአቸውን በመሰወር የቀረቡ መሆኑን ያሳያል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ምስክሮቹ የሰጡትን ቃል ስንመረምረው 1ኛ ምስክሩ ለመራጮች መደለያ በምርጫ አስፈፃሚዎች መሰጠቱን ይህ የተፈፀመውም በሾቢራካ ትምህርት ቤት ውስጥ መሆኑን ገልፀው ሪፖርት የተደረገላቸውን በተመለከተ በአባይነህና ሰላሙ ላንቲሶ የተነገራቸውን ሲያስረዱ አቶ ሰላሙ ላንቲሶ በሌሞ 01 የፓርቲው ተንቀሳቃሽ ወኪል መሆናቸውን ያስረዱ ቢሆንም ከዚህ ይልቅ በሌሞ 01 ምርጫ ክልል እጩ ተወዳዳሪ ሆነው ተመዝግበው መገኘታቸው የምስክሩን ቃልና ደረሰኝ የሚሉትን ሪፖርት አጠራጣሪ የሚያደርገው ነው፡፡ከመደለያ መስጠት፤የምርጫ ወረቀትን ደብቆ ከማስገባት እንዲሁም ተገቢነት ከሌላቸው መራጮች ጋር በተያያዘ በሄጦ ምርጫ ጣቢያዎች በተለይም ሄጦ 05፤06፤08 እና 09 ተፈፀሙ ያሏቸውን ከመግለፅ ባለፈ በቦርዱ ውሳኔ ላይ እንደተመለከተው በ43 እና ከዚያ በላይ በሆኑ የምርጫ ጣቢያዎች ላይ ድርጊቱ መፈፀሙን አላስረዱም፡፡

የፀጥታ ሀይሎች ፈፀሙት ካሉት በመራጮች ላይ ጫና የማሳደር ድርጊት ጋር በተያያዘ በሌሞ 01 በሙሉ ድርጊቱ እንደተፈፀመ ያስረዱ ቢሆንም ለዚህ ጥቅል መደምደሚያ መነሻቸው ምን እንደሆነ በምስክርነት ቃላቸው ላይ በግልፅ አላስረዱም፡፡ምስክሩ መረጃው ከ73 የምርጫ ጣቢያዎች ተቀማጭ ወኪሎቻቸውና ከ1 ጣቢያ ተንቀሳቃሽ ወኪላቸው የመጣ መሆኑን ያስረዱ ቢሆንም የወኪሎቹን ስም በመዘርዘር ሰላሙ ላንቲሶ (በሌሞ 01 ምርጫ ክልል እጩ ተወዳዳሪ ሆነው ተመዝግበው መገኘታቸው እንደጠበቀ ሆኖ) በ16 ምርጫ ጣቢያ፤አባይነህ አላቦ አንድ ምርጫ ጣቢያ እንዲሁም አዲሴ አውቶ ( በሶሮ 01 የምርጫ ክልል እጩ ተወዳዳሪ መሆናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ) በ6 የምርጫ ጣቢያ ወኪል መሆናቸውን ብቻ ማመልከታቸው



ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ

ይህም መረጃው ተዓማኒ ነው ቢባል እንኳ መረጃው በድምሩ የ23 ምርጫ ጣቢያ መሆኑን እያሳየ ከ73 የምርጫ ጣቢያ መረጃው መጣልኝ ማለታቸው ምንን መሰረት እንዳደረገ የምስክርነት ቃሉ አያሳይም፡፡

2ኛ ምስክርም ሄጦ በአምስት የምርጫ ጣቢያዎች ላይ ተፈፀመ ያሉትን ጥሰት ከማስረዳት ባለፈ በቦርዱ ውሳኔ ላይ እንደተመለከተው በ43 የምርጫ ጣቢያዎች ላይ ተፈፀሙ የሚባሉትን ከፍተኛ ጥሰቶች ማስረዳታቸውን የምስክርነት ቃሉ አያሣይም፡፡ በታችኛው አምቢቾ ምርጫ ጣቢያ 01 ምርጫው ያለምንም ሁከት ተካሂዶ ለመጠናቀቁ አቶ አሸናፊ በቀለ የተባሉ የ1ኛ መልስ ሰጪ ወኪል በቃለ ጉባዔው ላይ በመፈረም አረጋግጠው እያለ አቶ አዲሴ አውቶ በታችኛው አምቢቾ ጥሰት አለ በማለት ማስረዳታቸው ፤በተመሳሳይም በአምቢቾ ጎዴ ምርጫው በሰላም መጠናቀቁን አቶ ፈታሞ ኤርጊቾ የተባሉ የ1ኛ መልስ ሰጪ ወኪል በፊርማቸው አረጋግጠው እያለ በዚህ የምርጫ ጣቢያ ጥሰት አለ በማለት አቶ አዲሴ የምስክርነት ቃል መስጠታቸው የምስክሩ ቃልና በእለቱ በፓርቲው ታምኖ የተፈረመው ቃለ ጉባዔ የሚጋጭ መሆኑን ያሳያል፡፡

አቶ አዲሴ አውቶ በሶሮ 02 ምርጫ ክልል እጩ ተወዳዳሪ ሆነው እያለ ይህንን በወቅቱ የነበራቸውን ተሳትፎ በመደበቅ ምስክርነት ቃል መስጠታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በ42 የምርጫ ጣቢያዎች ተዘዋውሬ ታዝብኩ በማለት ማስረዳታቸው የማያሳምን ሆኖ እያለ ይህም የ1ኛ መልስ ሰጪ ምስክሮች 1ኛ መልስ ሰጪ ተፈፀሙ ያላቸውን ጥሰቶች አስመልክቶ ግልፅና አሳማኝ (Clear and Convincing) ማስረጃ አለማቅረቡን እያሳየ ከዚህ ባለፈ የቀረበው የፎቶ ማስረጃ አስረጂነቱ ምን እንደሆነ እንኳ በውሳኔው ላይ ሳያመለክት ቦርዱ በ43 የምርጫ ጣቢያዎች ጥሰት መፈፀሙ በ1ኛ መልስ ሰጪ ማስረጃዎች ተረጋግጧል በማለት መደምደሙ ተገቢውን የማስረጃ ምዘናና ምርምራ መርህ ያልተከተለ መደምደሚያ ላይ መድረሱን ያሳያል፡፡

1ኛ መልስ ሰጪ ጥሰቱ ተፈፀመ ባሉበት ጊዜ እዝያው ለሚገኘው ለምርጫ አስፈፃሚ ኮሚቴ እና በቅደም ተከተል ለሚገኙ የቅሬታ ሰሚ አደረጃጀቶች ሳያቀርብ መቅረቱ ለቦርዱ ቅሬታውን ማቅረቡ ከላይ እንደተመለከተው ይግባኝ የማቅረብ መብቱን የሚያሳጣው ባይሆንም ቅሬታውን በእለቱና በሰዓቱ በስፍራው ለሚገኘው የቅሬታ ሰሚ አካል ሳያስመዘግብ መቅረቱ 1ኛ መልስ ሰጪ ከጥሰቱ ጋር በተያያዘ ያቀረበው ክርክርና ማስረጃ ጊዜያዊ የምርጫ ውጤትን ተከትሎ የቀረበ ከማስረጃ ምዘና አነስተኛ ግምት የሚሰጠው ክርክርና ማስረጃ መቅረቡን የሚያሳይ ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የምርጫ ውጤት ሊቀይር የሚችል ቁጥር ያለው መራጭ ድምጽ እንዳይሰጥ ከተከለከለ ወይም ተገዶ ለአንድ ወገን እንዲሰጥ ከተደረገ ወይም የፈለጉትን ፓርቲ ሆነ እጩ እንዳይመርጡ ከተደረገ፣ የምርጫውን ውጤት ሊቀይር የሚችል ቁጥር ያለው ድምጽ መስጫ ወረቀት የጠፋ፣ የተቀደደ፣ የተበላሸ በመሆኑ ለመቁጠር የማይቻል ድምጽ እንዲሆን ከተደረገ፣ የተሰጠው ድምጽ ለመስጠት ከተመዘገበ



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ፍርድ ቤት The Federal Supreme Court Federal Democratic Republic of Ethiopia
... ጠቅላይ ፍርድ ቤት ትክክለኛ ግልባጭ
8/3/2014

መራጭ በላይ በልጦ የተገኘ እንደሆነና በድጋሚ ቆጠራ በማድረግ ካልተስተካከለ፣ በምርጫ ክልሉ በሚገኙ በአብዛኛው የምርጫ ጣቢያዎች ላይ መራጮችን ወይም ተወዳዳሪዎችን ወይም ወኪሎቻቸውን ወይም የምርጫ ቦርድ አስፈጻሚዎች ላይ ፍርሃት እና መሸማቀቅ የሚፈጥር የኃይል ተግባር ከተፈጸመ፣ ከላይ ከተጠቀሱት ሁኔታዎች ውጭ የተወሰኑ ምርጫ ጣቢያዎች ወይም ምርጫ ክልሎች ላይ የተረጋገጠ ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ በመከሰቱ ምክንያት የተሰጠውን ድምጽ መቁጠር ወይም ውጤቱን ማወቅ ካልተቻለና አሸናፊውን መለየት የማይቻልበት አግባብ ሲያጋጥም ምርጫ ቦርድ የተፈጸመው ስህተት የምርጫ ውጤቱን የሚያዛንፍ ነው በማለት ድጋሚ ምርጫ እንዲካሄድ ብሎ ለመወሰን እንደሚችል በምርጫ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 15/2013 አንቀጽ 7(3) የተመለከተ ሲሆን በይግባኝ ባይና በ1ኛ መልስ ሰጪ መሃል ለክልል ምክር ቤት 70,414 እንዲሁም ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 74,058 የድምፅ ልዩነት እያለ 2ኛ መልስ ሰጪ ከነዚህ ከላይ ከተመለከቱት ሁኔታዎች የትኛው ጥሰት እንደተፈፀመ በግልፅ ሳያመለክትና ይህ የተፈጠረው ጥሰትም በምን አግባብ የምርጫውን ውጤት ሊቀይር የሚችል ጥሰት እንደሆነ ሳያመለክት የምርጫ ክልሉ ውጤት እንዲሰረዝና በድጋሚ ምርጫ እንዲካሄድ መወሰኑ ተገቢውን የማስረጃ ምዘናና ምርምራ መርህ ያልተከተለ እና ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን የምርጫ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 15/2013 አንቀጽ 7(3) መሰረት ያላደረገ ሆኖ ስላገኘነው የሚከተለውን በአብላጫ ድምጽ ወስነናል፡፡

## ውሳኔ

1. የኢትዮጲያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ጥቅምት 01 ቀን 2014 ዓም የሌሞ 01 የምርጫ ክልል ውጤት እንዲሰረዝና በድጋሚ ምርጫ እንዲካሄድ የሰጠው ውሳኔ በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. 1ኛ መልስ ሰጪ በሌሞ 01 የምርጫ ክልል ውጤት እንዲሰረዝና በድጋሚ ምርጫ እንዲካሄድ ያቀረበው አቤቱታ በተገቢው ማስረጃ ተደግፎ ያልቀረበና የምርጫ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 15/2013 አንቀጽ 7(3) መሰረት ያላደረገ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኙ በይግባኝ ክርክሩ ምክንያት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

<u>ጉዳዩ ውሳኔ ስላገኘ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡</u>

የማይነበብ የሁለት ዳኞች ፊርማ አለበት

ም/ቶ

Federal Supreme Court
8/7/2014

## የልዩነት ሃሳብ

ሥሜ በተራ ቁጥር ሦስት ላይ የተሰየምኩት ዳኛ ከአብላጫው ሃሳብ የተለየሁበትን ምክንያት እንደሚከተለው አስፍሬያለሁ፡፡

ይግባኙ የቀረበው በኢትዮጵያ መስከረም 20 ቀን 2014 ዓም በተደረገው 6ኛው አገር አቀፍ ምርጫ በሌሞ 01 ምርጫ ክልል በተለያዩ የምርጫ ጣቢያዎች ከድምፅ አሰጣጥ፤ቆጠራ እና ውጤት መደመርን በሚመለከት የተለያዩ ጥሰቶች ተፈፅመዋል በማለት ያቀረበውን አቤቱታ እና ማስረጃዎች በመመርመር 2ኛ መልስ ሰጭ የሆነው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በሰጠው ውሳኔም በሌሞ 01 የምርጫ ክልል ውጤት እንዲሰረዝና በድጋሚ ምርጫ እንዲከናወን መወሰኑን በመቃወም ይግባኝ ባይ ዝርዝር ቅሬታ በማቅረቡ ነው፡፡ 2ኛ መልስ ሰጭ በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1133/2011 አንቀጽ 7 ላይ ዝርዝር ሥልጣን የተሰጠው ሲሆን ከእነዚህም መካከል ፓርቲዎችን መመዝገብ፣ መከታተልና መቆጣጠር፣ ምርጫ ማካሄድና ማስፈጸም በሕግ የተሰጠው አስተዳደራዊ ሥልጣኑ ሥር የሚወድቁ ጉዳዮች ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ስነምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 155 እና ተከታይ ድንጋጌዎች አግባብ በድምጽ ቆጠራና ውጤት ላይ ቅሬታ ያላቸው አካላት አቤቱታቸውንና ማስረጃዎችቻውን አቅርበው ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጉዳዩን መርምሮ የሚሰጣቸው ውሳኔዎች የዳኝነት ነክ አካል ሥልጣን የተሰጠው መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ የዳኝነት ነክ አካል በሕግ በግልጽ የተለዩ ውስን ጉዳዮችን የሚመለከት ዳኝነት ሰጭ አካል እንደመሆኑ መጠን መደበኛው ፍርድ ቤት የሚመራበት ሥርዓትን መከተል ሳይገባው በሚወጣለት ልዩ ሥነ-ሥርዓት ተከትሎ ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ነገር ግን ማንኛውም የዳኝነት አካል ሊከተለው የሚገባ የዳበረ የዳኝነት አሰጣጥ ዝቅተኛ መስፈርቶች አሉ፡፡ ዋና ዋናዎቹም የቀረበለትን ጉዳይ ለመመልከት ሥልጣን ያለው መሆኑ፣ ጉዳዩን ያቀረበው ሠው አቤቱታውን ለማቅረብ መብት ያለው መሆኑ (standing right)፣ መብቱ የበሰለ ስለመሆኑ (ripeness)፣ የግራቀኙን ወገን የመደመጥ መብት (basic due process) ያከበረ መሆንና ውሳኔው የተመሠረተው በተጠየቀው ዳኝነት አግባብ መሆን ናቸው፡፡

ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ቀን 8/7/2014

ን ባይ ቅሬታ በቀረበበት ምርጫ ክልል ላይ ጊዜያዊ አሸናፊ መሆኑ የታወቀ በመሆኑ ውጤቱን ቀሪ ለማድረግ አቤቱታ ሲቀርብ አቤቱታውን የማወቅና በክርክር ሂደቱ የመደመጥ መብት አለው። የሕግ ሥርዓት ሂደት (due process of law) መሟላት ከፍርድ ሊቀድም ይገባል የሚለውን መርህ የሚከተል ሲሆን በፍትሐ ብሔር ሆነ በወንጀል ክርክር ሂደቶች ያለ መብት ነው። ከተከሳሽ አኳያ በነፃና ገለልተኛ የዳኝነት አካል የመዳኘት፣ ክሱን የማወቅ መብት፣ የመደመጥ መብት (መከላከያ ክርክር ማቅረብ፣ የከሳሽን ማስረጃ የማወቅና በማስረጃው ላይ ክርክር ማቅረብና ምስክሮችን የመጠየቅ መብት እና የራሱን ማስረጃ የማቅረብ መብትን ያካትታል።)፣ የሚሰጠው ውሳኔ በሕግና በምክንያት ላይ የተመሠረተ ብቻ እንዲሆን እና ሌሎች ተያያዥ መብቶችን ያካተተ ሰፊ መብት ነው። አቤቱታን የማሰማት እና የቀረበውን ቅሬታ በማስረጃ ለማረጋገጥ ማስረጃ የማቅረብ መብት በሥነ-ስርዓታዊ የሕግ ሥርዓት ሂደት ውስጥ ያለ መብት ነው። የመደመጥ መብት ካልተከበረ፤ ቅሬታውንና ማስረጃውን እንዳያቀርብ ከተደረገ፣ ቅሬታውን የሚሰማው አካል ክርክሩን ከግራቀኙ ተከራካሪ ወገኖች ካላደመጠ ደግሞ ለእውነቱ የቀረበና ትክክለኛ ፍትሕ መስጠት አይቻልም።

2ኛ መልስ ሰጭ በበኩሉ የምርጫ ቅሬታ አቀራረብ ሥርዓትና የምርጫ ባሕሪው ይግባኝ ባይን እንድጠራ አያስገድደኝም በማለት ተከራክሯል። የምርጫ ውጤትን መሠረት ያደረገ ክርክር ከባሕሪው በመነሳት በአጭር ጊዜ ሊከናወን የሚገባ ነው። ይሕ ማለት ግን የዜጎች ወይም የምርጫ ተወዳዳሪዎች መሠረታዊ መብት ጊዜውን ምክንያት ተደርጎ ሊጣስ ይገባል ማለት አይደለም። ክርክሩ የሚወስደው ጊዜ ማሳጠር ማለት መሠረታዊ የሆነውን መብት መልሶ መቀማት ሊያስከትል አይችልም። አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 155(4) የመጨረሻውን ዓረፍተ-ነገር ስንመለከት ለመወሰን የሚያስፈልጉ ማስረጃዎችን አስቀርቦ ይመረምራል (review all necessary evidences) ማለቱ ሲታይ፤ በሥነ-ሥርዓት ሕጉ ለይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በአንቀጽ 327(3) እና 345 መሠረት የተሰጠው ማስረጃን የማስቀረብ ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በቦርዱ ደረጃ የቀረቡ ማስረጃዎችን ከቦርዱ በማስቀረብ እንዲመለከት የሚገልጽ እንጂ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ እንደሚመለከት ፍርድ ቤት የተከራካሪን ማስረጃ እንዲሰማና ፍሬ ነገር እንዲያጣራ የሚያዝ አይደለም። ፍርድ ቤቱ የሚወስንበት ጊዜ አንድ ወር የተሰጠውም በመርሕ ደረጃ አዲስ ክርክርና ማስረጃ አይቀርብም የሚለውን ታሳቢ ማድረጉን መገንዘብ ያስፈልጋል። ይግባኝ ባይ በምርጫ ቦርድ ደረጃ በክርክሩ ካልተሳተፈና ከውሳኔ በኋላም አቤቱታ ሲያቀርብ ቦርዱ አቤቱታውን ለመቀበል ካልቻለ ያለው መብት ለዚህ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ሲሆን ይሕ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ምርጫው ላይ ጥሰት አለበት ወይስ የለበትም የሚለውን ለመወሰን ምርጫ ቦርድ በሥር ከሰማቸው የ1ኛ መልስ ሰጭ ማስረጃ በተጨማሪ

ባኝ ባይን ማስረጃ መሰማት ስላለበት ውጤቱ ደግሞ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱን አዲስ ማስረጃ የሚቀበልና የሚያከራክር ችሎት (trial bench) ያደርገዋል። ይሕም ከምርጫ ቦርድ በተለየ ፍርድ ቤቱ በመደበኛና ጥብቅ የሥነ-ሥርዓት ሕጉ የሚመራ በመሆኑ ክርክሩ ጊዜ እንዲወስድ ያደርገዋል። ስለሆነም 2ኛ መልስ ሰጭ ይግባኝ ባይን በክርክሩ በምርጫ ቦርድ ደረጃ ማሳተፍ ጊዜ የሚወስድና የምርጫ ባሕሪን ያገናዘበ አይደለም በሚል የሚያቀርበው ክርክር ተገቢነት የሌለው መሆኑን ያሳያል።

ሌላው የ2ኛ መልስ ሰጭ ክርክር ይግባኝ ባይ ያለው መብት ይግባኝ የማቅረብ መብት ነው የሚል ነው። በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 155(4) ላይ በምርጫ ቦርድ ውሳኔ ቅር የተሰኘ <u>አቤቱታ አቅራቢ</u> (ሠረዝ የተጨመረበት) ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቤቱታውን/ይግባኝ ማቅረብ ይችላል የሚል ሲሆን በቦርዱ ውሳኔ በቀጥታ ይግባኝ ማቅረብ የተፈቀደለት አቤቱታ አቅርቦ በቦርዱ ውሳኔ ያልተስማማን ተከራካሪ የሚመለከት ነው። በቦርዱ ደረጃ አቤቱታ ያላቀረበ ወይም በክርክሩ ያልተሳተፈ ወገን የምርጫ ቦርድ ውሳኔ መብቱ ቢነካበት መብቱን የሚያስከብርበት ሥርዓት ምንድን ነው የሚለውን ሕጉ በቀጥታ አይመልስም። የምርጫ ውጤት ጋር በተያያዘ የሚነሳ ክርክር በፍትሐ ብሔር ክርክር ውስጥ የሚመደብ ሲሆን የፍትሐ ብሄር ክርክር ደግሞ ተከራካሪን የተከለተ (party doctrine) ነው። ይግባኝ ለማለት በክርክሩ ተሳታፊ መሆንን ይጠይቃል። ምርጫ ቦርድ እንደ የዳኝነት ነክ አካል ሆኖ ባስተናገደው የምርጫ ውጤት ጋር በተያያዘ ለቀረበ ክርክር በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 40(2) መሠረት ይግባኝ ባይን በክርክሩ በመጥራት ማሳተፍ ሲገባውና በክርክሩ ጊዜ ካልተሳተፈም ውሳኔው መብቱን ይነካል በማለት ክርክር ለማቅረብ ሲጠይቅ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.358 መሠረት ተቀብሎ ማስተናገድ ሲገባው መከልከሉ ስህተት ያለበት በመሆኑ ጉዳዩ ለ2ኛ መልስ ሰጭ ተመልሶለት የይግባኝ ባይን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ እንዲወስን ሊደረግ ይገባል። ይህ ባልሆነበትና ምርጫ ቦርድ በሰማቸው ምስክሮች ግልጽ ጥሰት መኖሩ በተገለጸበት ሁኔታ ምስክሮች በምርጫ ክልል ቋሚና ተንቀሳቃሽ ወኪል ካልሆኑም ትክክለኛ ፍትሕ ለመስጠት ሲባል ወኪሎች ቀርበው እንዲሰሙ ተደርጎ እና የይግባኝ ባይም ማስረጃ አብሮ ተሰምቶ ሊወሰን ሲገባ 2ኛ መልስ ሰጭ የሰጠው ውሳኔ ቀሪ መደረጉ የሕግ ስሕተት ያለበት ነው በማለት በሃሳብ ተለይቻለሁ።

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

ም/ቶ